# ስለ 45+ ዩኒቨርሲቲዎች ሙሉ መረጃ ከ ቀሰም Academy

© ቀሰም Academy

JOIN US ON TELEGRAM

@QesemAcademy

መረጃው ምን ያካትታል

ስለ እያንዳንዱ ዮኒቨርሲቲ መገኛ አድራሻው የየአየር ሁኔታው ፤ በውስጡ የሚገኙ ካንፓሶች ብዛት ፤ የሚሰጡት ፊልድ ፤ ስለ ካፌ ምግብ ሁኔታ ፤ በሳምንት ውስጥ ካፌ የሚሰጡ ምግቦች ዝርዝር ስኬጁል ፤ ከካፌ ውጪ ስለሚገኙ ምግቦች እና ዋጋቸው ፤ ስለ ዶርም ምቹነት ፤ ስለ ግቢው ድንገተኛ ክሊኒክ ፤ ስለ ሽንት ቤት ፤ ስለ ውሃ እና መብራት ፤ በግቢው ስላለ ዕቃ ስርቆት፤ስለ ሃይማኖታዊ ተቋማት እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች የሚመልስ ዝርዝር መረጃዎች ይዟል!

የዮኒቨርሲቲዎቹ ዝርዝር በቅደም ተከተል ፡-

❶ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

❷ ጅማ ዩኒቨርስቲ

❸ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ

❹ ጎንደር ዩኒቨርስቲ

❺ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ

❻ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ

❼ መቀለ ዩኒቨርስቲ

❽ ሀረማያ ዩኒቨርስቲ

❾ ወሎ ዩኒቨርስቲ

❿ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ

⓫ አርሲ ዩኒቨርስቲ

⓬ ዲላ ዩኒቨርስቲ

⓭ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

⓮ ወልድያ ዩኒቨርስቲ

⓯ ደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ

⓰ ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ

⓱ ደባርቅ ዩኒቨርስቲ

⓲ መቅደላ አምባ ዩኒቨርስቲ

⓳ አምቦ ዩኒቨርስቲ

⓴ ቀብሪ ዳሀር ዩኒቨርስቲ

21. ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርስቲ

22. ሰላሌ ዩኒቨርስቲ

23. ደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ

24. ራያ ዩኒቨርስቲ

25. ወለጋ ዩኒቨርስቲ

26. መቱ ዩኒቨርስቲ

27. አክሱም ዩኒቨርስቲ

28. አዲግራት ዩኒቨርስቲ

29. ሚዛን-ታፒ ዩኒቨርስቲ

30. ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ

31. ቦንጋ ዩኒቨርስቲ

32. ወራቤ ዩኒቨርስቲ

33. ጂንካ ዩኒቨርስቲ

34. ጋምቤላ ዩኒቨርስቲ

35. እንጅባራ ዩኒቨርስቲ

36. ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ

37. ሰመራ ዩኒቨርስቲ

38. ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ

39. አሶሳ ዩኒቨርስቲ

40. ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ

41. ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

42. ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርስቲ

43. ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ

44. መዳ ወላቡ ዩኒቨርስቲ

45. አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## 1)  አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አድራሻ....

በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ውስጥ ይገኛል ፡፡

የአየር ሁኔታ ...

የመጀመሪያዎቹ ወራቶች መጠነኛ ብርዳማ ሆነው ወደ ኋላ ላይ ግን ሞቃታማ የአየር ንብረት አለው ፡፡

የካንፓሶች ብዛት

በጣም ብዙ ማለትም አስራ ሰባት ይደርሳሉ ፡፡ እያንዳንዱ ካንፓስ የተለያየ ፊልድ ይሰጣል ፡፡

ያሉት ካንፓሶች ፡-

6 ኪሎ ፣

5 ኪሎ ፣

4 ኪሎ ፣

ሜክሲኮ ፣

ልደታ ፣

18 ማዞሪያ

ጥቁር አንበሳ ( hospital)

ቃሊቲ ፤

ቢሾፍቱ (ደብረዘይት) ፤

ላምበረት ......ካንፓሶችን ያካትታል ።

በካንፓሶች የሚሰጡ ፊልዶች

6 kilo

ለሶሻል ተማሪዎች ብቻ የሶሻል ዘርፍ ትምህርቶችን ይሰጣል ።

5 kilo

ለኢንጂነሪግ ( Software , electrical , biomedical , mechanical , civil , chemical ..የሚሰጥበት ካንፓስ ነው ።

biomedical engineering ከሚሰጥባቸው ጥቂት ዩንቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው።

4 kilo

በዚ ካንፓስ computer science እና computer engineering ይሰጣል ።

18 ማዞሪያ

የሜዲሲን ዘርፎች በ Other health የሚካተቱትን ይሰጣል ።

ጥቁር አንበሳ

ይህ ካንፓስ አንጋፋ ሲሆን በውስጡም የMedicine ኮርስን ይሰጣል ፤ ተማሪዎች አፓረንትም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ይወጣሉ ።

ላም በረት

በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ላይ ብቻ አተኩሮ የሚሰራ ካንፓስ ነው ፤ AASTU የሚገኝበት ሲሆን APPLIED እና Enginering ኮርሶችን ይሰጣል ።

ልደታ

በልደታ ካንፓስ  የሚሰጡት ፊልዶች architecture ፤ cottom ፤ urban plannig እና የመሳሉትን ያካትታል ።

ሜክሲኮ

ይህ ካንፓስ የcommerce ግቢ ነው ። ( marketing management , business administration, management የሚሰጥበት ካንፓስ ነው ።)

ሰፈረ ሰላም

የጤና ዘርፍ ግቢ ነው ፤ ሜዲስን ነርሲንግ እና የመሳሰሉት ወደ ጥቁር አንበሳ 3ተኛ አመት ላይ ከመሄዳቸው በፊት የማሩበት ግቢ ነው ።

ቢሾፍቱ ካንፓስ

AAU ደብረዘይት ላይ Veterinary medicine & Science collage አለው ። ደብረዘይት ነው የሚገኘው ካንፓሱ በጤና እና ሳይንስ ዘርፍ ይሰጣል ..!

ለኢንጅነሪግ ተማሪዎች፥

➡️ የdrawing መሳሪያዎች መያዝ አለባችሁ

➡️ Mathematics and Mechanics Statics guide books ይዛቹህ ብትሄዱ መልካም ነው ።

የካፊው ምግብ

ምግቡ ለክፉ የሚሰጥ አይደለም ከሌሎች ዮኒቨርሲቲዎች የተሻለ ነው ፤ በተለይ ደግሞ ሰፈረ ሰላም ካንፓስ ደስ የሚል ነው ።

በሳምንት ውስጥ ካፌ የሚሰጡ ምግቦች ዝርዝር ስኬጁል

ከሌሎች ዮኒቨርስቲዎች የተለየ አይደለም ቁርስ ፍርፍር ፤ ሩዝ ፤ ሻይ በዳቦ ፤ ስልስ ይቀርባል ፤ ምሳ እና እራት በሳምንት 2-3 ቀን ስጋ ምሳ እና እራት ይኖራል ፤ ሽሮ ፤ ምስር ፤ አታክልት የመሳሰሉት ምግቦች ይቀርባሉ ። (በፎቶ የምግቡን ጥራት ማየት ይቻላል)

ከካፌ ውጪ ስለሚገኙ ምግቦች እና ዋጋቸው

ከሌሎች ግቢዎች የተለየ አይደለም ነገር ግን 4 ኪሎ ግቢ ምግብ ከሚታሰበው በላይ ቅናሽ ነው ። ዋጋቸው ከታች ተቀምጧል ...!

ቀላል ምግቦች ፓስታ ፍርፍር... etc 20 -30 ብር

ከባድ ምግቦች እንቁላል ፤ ስጋ ..etc 30-50 ብር

ሻይ እና ቡና ...etc 2-4 ብር ይሆናል ።

የሎከር ነገር

ሎከር በጣም አስቸጋሪ ነው ፤ በዶርም ውስጥ አንድም የሚሰራ ሎከር ማግኘተ ይከብዳል ። አብዛኛው ተበላሽቷል አይሰራም ።

ውሃ

ውሃ በተደጋጋሚ ይጠፋል ፤ በተለይ ደሞ የዕረፍት ቀናት ለአንድ ሰዓት ብቻ ተለቆ ይቆማል ፤ ከተማዋ ላይ የውሃ እጥረት ስላለ ግቢ ውስጥም የተለየ ነገር የለም ..!

...ሽንት ቤት ...

እንደ ካንፓሶቹ ቢለያይም አብዛኛው ግን በጣም አሪፍ የሚባል ነው ፤ በተለይ 4 ኪሎ በየቦታው ይገኛል ፤ የሚያስከፋ ነገር የለውም ሻል ያለ ነው ።

በግቢው ስላለ የዕቃ ስርቆት፡-!

እንደካንፓሶቹ ቢለያይም ግርግር ፤ ረብሽ የሚባል ነገር ስለሌለ የስርቆት ነገር በጣም rare ነው ፤ ቾልተኛ ካልሆነ ስርቆቶ ብዙ የሚያሳስብ ነገር አይደለም ።

የሃይማኖታዊ ተቋማት ፡-

በብዙዎቹ ካንፓሶች በአቅራቢያቸው መስኪድ እና ቤተስኪያን ስላለ ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን ለመከውን አያዳግትም ።

## 2)JIMMA UNIVERSITY

አድራሻ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከሆነችዉ ከአድስ አበባ ደቡብ ምዕራብ በኩል የሚትገኝ ሲሆን ከአድስ አበባ እስከ ጅማ 390 km አከባቢ ነዉ።

የአየር ሁኔታ

ሞቃታማ ፥ ከአዳማ እና ከመሰል ሞቃት ሃገሮች ለሚመጡ ተማሪዎች ሙቀቱ ምንም ዓይነት ተጽእኖ የለውም እንዲያውም ሊበርዳቸው ይችላል፤ በግልባጩ ደግሞ ከብርዳማ አከባቢ ለሚመጡ ተማሪዎች የሙቀቱ መጠን ከፍ ያለ ይሆንባቸዋል ።

ለማንኛውም ቀለል ያሉ ልብሶችን ይዛቹህ ብትሄዱ መልካም ነው።

ስለ ዮኒቨርስቲው

ድሮም ጀምሮ የፍቅር ከተማ ተብሎ በሚጠራዉ በጅማ ከተማ የሚገኝ አንጋፋና ለኑሮም ሆነ ለትምህርት ከየትኛዉም ዩኒቨርሲቲ የተሻለ ነዉ ብለን የሚናስበዉ ዩኒቨርሲቲ ነዉ። ጅማ ታርካዊና አንጋፋ በሆኑ በንጉስ አባጅፋር ታርክ የታወቀች ከተማ ስትሆን ዩኒቨርሲቲዉ ለከተማ ብዙም ሳይርቅ በከተማ ዉስጥ ነዉ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ይገኛል። ሌላዉ እና በጣም ደስ የሚል ታርካዊ ቦታ ቢኖር ንጉስ አባጅፋር ቤተመንግስት የሚገኘዉ ከዋናዉ ግቢ ብዙም ሳይርቅ መገኘቱ ነዉ። ለጉብኝት በፈለጋችሁ ጊዜ ሁለ መዝናናት የሚያስችል ቦታ ነዉ። በጅማ ዩኒቨርሲቲ በጣም የሚያማምሩ ህንፃዎች ከመኖራቸዉ ባሻገር ለመማርም በጣም ምቹ የሆኑ ህንፃዎች ናቸዉ። ጅማ ዩኒቨርሲቲ በጣም በፍጥነት እያደገች ትገኛለች።

የካንፓሶች ብዛት

በጅማ ዩኒቨርሲቲ አራት Campus ያለ ስሆን ከቅርብ ጊዜ በኋላ አንድ አድስ campus ስራ ይጀምራል ተብሎ ይገመታል።

የአራቱ campuses ስማቸዉም እንደሚከተለዉ ነዉ፦

# ዋና ጊቢ ( Main campus)..

በዋና ግቢ የሚገኙ ኮሌጆች ፦

# ጤና እንስቲትዩት

# ህግና አስተዳደር ኮሌጅ

# የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ

#ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ እና

# ስነ ባህሪ ኮሌጅ ናቸዉ።

ቤኮ ኮሌጅ ( College of business& economics) ከዋናዉ ግቢ ትንሽ የሚርቅና በመካከላቸዉ ትልቅ መንገድ ያለ ስሆን ዋናዉንና ቤኮ ግቢዉን የሚያገናኝ ትልቅ ድልድይ ይገኛል። ከዚህ የተነሳ የዋና ግቢ ተማርዎችም ሆነ የቤኮ ( college of business& economics ) ተማርዎች በድልድዩ በኩል ያለምንም መንገድ ችግር ይመላለሳሉ።

# የቴክኖሎጂ ግቢ የእንጂነርግ ተማሪዎች እና የcomputer

science ግቢ ሲሆን ለመማርም ለመኖርም ምቹና በጣም አስደናቂ የሆኑ ህንፃዎች ያሉበት ግቢ ስሆን በመጀመሪያ ጊዜ የህንፃዎችን አሰራር ያዩ ሰዉ እዉነትም ይህ ህንፃ የእንጂነሮች ስራ ነዉ ብሎ ከማድነቅ ወደኋላ አይልም። የቴክኖሎጂ ግቢ ከዋናዉ ግቢ የ 5 ብር መንገድ ስሆን ከጅማ ከተማ ከመርካቶ የ 3 ብር መንገድ ነዉ።

4# የግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ፦ የሚገኘዉ ከቴክኖሎጂ ግቢና ከዋና ግቢ መሃል ይገኛል። የግብርና እና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ከዋናዉ ግቢ የ5ብር መንገድ ስሆን ከመርካቶ የ3 ብር መንገድ ነዉ። (በታክሲ)

በእያንዳንዱ ግቢ አንደኛ አመት ተማሪዎች ይመደባሉ ፤ የጂማ ዩኒቨርሲቲ ብሎኮች በጣም የሚያማምሩ ናቸው ። ትምሮ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ትንሽ ከበድ ሊልባቹህ ስለሚችል በግቢው ምቾት እንዳትታለሉ ።

የካፌ ምግብ

የምግብ ነገር ከሌሎች ግቢዎች በሚመጡ ተማሪዎች የተመሰከረለት ነው። የግቢ ካፌ በጣም ተስማሚ ከመሆኑ የተነሳ non ካፌዎች ቁጥር አናሳ ነው ።

ምግቡ Normal ነው አንዳንድ ምግቦች ሊደብሩ ይችላሉ በተለይ ለፍሬሽ ቢሆንም ግን ጨጓራ ምናምን አይነካም።

ከካፌ ውጪ ስላሉ ምግቦች

በካፌው በተጨማሪ ግቢ ውስጥ እና ከግቢ ውጭ ያሉ ብዙ አማራጮች አሉ። ከግቢ ውጭ ያሉ ብዙ ምግብ ቤቶች አሉ ፥ በአይነትም በጥራትም አሪፍ የሚባሉ። በጣም የሚገርማቹህ ውድ የሚባልው ምግብ 3p ብር ነው ።

ፓስታ ፣ አይነት ፣ ሽሮ ምናምን ከግቢ ውጭ 20ብር ሲሆኑ ግቢ ውስጥ ደግሞ 25 ብር ናቸው።

ሻይ ሁለት ብር ሲሆን ቡና ደግሞ 3 ብር ነው። ለነገሩ ብዙም አይገርምም ሀገሩ ጅማ እኮ ነው በቡናማ አይታሙም። ከግቢ

ውጭ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን ማግኘት ይቻላል፤ ሙዝ ፣ ብርቱካን፣ አቩካዶ ምናምን ነፍ ነው ፤ ሌላም የተለያዩ ጁስ ቤቶች ይገኝሉ ፥ ጁስ 15 ብር ነው ።

## ውሃ መብራት እና WIFI

የብዙ ግቢዎች ችግር የሆነው የውሃ ጉዳይ ነው፤ ውሃ ጅማ ውስጥ ለአንድ ቀን ጠፋ ማለት ኒዎርክ መብራት ጠፋ ማለት ነው። የውሃ ችግር ጅማ ውስጥ የለም ማለት ይቻላል እንዳያሳስባቹህ ግን ሙሉ ለሙሉ አይጠፋም አይባልም ግን በዛ ቢባል ለአንድ ቀን ነው ።

መብራት ኖርማል ነው አንዳንዴ ብቻ ይጠፋል ፤ WIFI ለክፉ አይሰጥም አሁን ላይ መሻሻል እያሳዮ ነው ።

በተረፈ ጅማ ዩኒቨርሲቲ በሀገራችን ቀዳሚ ከሚባሉት ዩንቨርሲቲዎች ግንባር ቀደም በመሆኑ ብዙ አስቸጋሪ ነገር አያጋጥማችሁም ።

የሸንት ቤት

በብዙ ግቢዎች እንደተለመደው ትንሽ የሚያስቸግር ነገር ቢኖረውም ከብዙ ካንፓሶች የተሻለ ነው ።

## 3)አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዮኒቨርሲቲ

አድራሻ

በበረሃማዋ ከተማ በስምጥ ሸለቆ ዕንቁዋ በአዳማ ከተማ የሚገኝ አሪፍ ዮኒቨርሲቲ ነው ።

የአየር ሁኔታ

ሞቃታማ በተለይ በቀኑ ክፍለ ጊዜ ትንሽ ይሞቃል ፤ ይህን እንጂ ማታ ማታ ደግሞ ያልተጋነነ ብርድ ስለሚኖር ሹራብ ነገርም ያስፈልጋቹሃል ።

የካንፓሶች ብዛት

በውስጡ ያለው ግቢ አንድ ለናቱ ነው አንድ ብቻ ነው ።

የሚሰጡ Fields and Departments

ASTU ላይ ብዙዎቻቹህ እንደምታውቁት ሁለት የትምህርት

መስኮች ብቻ ይገኛሉ።

➡ Engineering &

Applied science ናቸው ።

ከሌላው ግቢ ትንሽ ለየት የሚያደርገው pre- engineering የሚያስተምረው ሁለት ሴሚስተር መሆኑ ነው ( department and school የምትመርጡት ሁለተኛ አመት ላይ ነው ማለት ነው ።)

Pre-engineering courses

► -General Chemistry(    )

► - General Physics 1

► - Applied Maths 1

► - Communicative english.

► - Introduction to computing( Python).

► - Civic or Logical reasoning.

► - HPE( 0 ch)

Second semister courses :-

⏭ - Applied Maths 2

⏭ - Technical drawing

⏭ - General physics 2

⏭ - Computing ( c++)

⏭ - English writing

⏭ - Civic or Logic

⏭ - HPE(0 ch)

Under Applied science pre-engineering courses :-

Almost the same as Engineering except one course

Departments of Applied Natural Sciences are :-

Applied Biology

. Applied Chemistry

Applied Geology

Applied Mathematics

Applied Physics

Under Engineering there are 3 schools :-

1. Electrical
2.Mechanical
3.Civil

Under electrical engineering or CSE there are 3 streams :-

A) Electrical and computer engineering

B) Electronics and communication engineering

C) Power and control engineering

Under Mechanical engineering

A. Chemical

B. Mechanical

C. Material

Under civil and arc school.:-

A.Architecture

B. Civil

C. Water resource management and hydrolic

Engineering

D. Geomatics (በቅርብ የሚጀመር ....!)

Note :-

Engineering ላይ Aerospace engineering and software engineering አሁን ላይ አይሰጥም ። በነገራቹህ ላይ የመግቢያ ፈተናው ብዙም አይከብድም፤ ፈተናው ከEntrance exam ጋር ተመሳሳይነት አለው።

Content of exam subjects are

- ► Chemistry
- ► Biology
- ► Mathematics
- ► Physics and
- ► English

የካፌ ምግብ

አንደኛ ነው ምንም አይወጣለትም ፤ በቃ ምርጥዬ ነው ለማለት ቢከብድም የእናታቹሁ ሽሮ ብዙም ትዝ አይላችሁም ።

ከካፌ ውጪ ያሉ ምግቦች

የምግብ ቤቶች ዋጋ ከ25-40 ብር ባለው range ይጠቃለላሉ። አሪፍ የሚባል ምግብ ያቀርባሉ ...!

አዲስ ነገር

ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገባቹህ ደግሞ አሪፍ ሽልማት ይበረከትላቹሃል ፤ በ2011 ከ3.76 በላይ ላመጡ 59 ተማሪዎች PC ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል። እምናና ካቻምናም በተመሳሳይ ብዙ ተማሪዎች ተሸልመዋል ፤ ከ3.5 በላይ ያመጡም የተሸለሙበት ጊዜ ነበር ። ብቻ እናንተ ጠንክሩ እንጂ ለሽልማቱ

አለንላቹህ ። ይሄ ነገር 2012 ጀምሮ ቆሟል ይቀጥላል ተብሏል ።

ሌላም surprise አለ Engineering ለምትገቡ የአምስት ዓመቱን ትምህርት በአራት አመት የመማር ዕድል ሊያጋጥማቹህ ይችላል ግን በጣም ትልቅ ጥረት ያስፈልጋል (ፈተና አለው) ለApplied science ተማሪዎችም የአራት ዓመቱን ትምህርት በሶስት ዓመት ማጠናቀቅ የሚችሉበት መንገድ በተመሳሳይ መልኩ ማለትም በቅድመ ፈተና ተፈትነው በማለፍ ብቻ pre Engineering ሳይማሩ መመረቅ ይችላል።

ውሃ ፤ መብራት እና wifi

ምንም አያሳስብም ትንሽ ውሃው ሙቅ ነው እንጂ ሌላ ጣጣ የለም ፤ WIFI በሽ ነው .....!

ሽንት ቤት

ምርጥዬ ነው ፤ በቃ አያሳስብም የገነት ቁልፍ በሉት ...!

አድራሻ

## 4)ጎንደር_ዩኒቨርሲቲ

አድራሻ

ጎንደር ከአዲስ አበባ በ727km ርቀት ላይ ትገኛለች። ከአዲስ ጎንደር በሀገር አቋራጭ ባስ ማለትም ሰላም ባስ ምናምን ከተጓዝን በአንድ ቀን እንደርሳለን። ወይም ደግሞ ከአዲስ አበባ ከመናሀርያ ወደ ባህርዳር ተጉዘን ከዛም በባህርዳር አድረገን ወደ ጎንደር መምጣት እንችላለን።፤ ነገር ግን የመጀመሪያውን ምርጫ ብትጠቀሙ ይሻላል፤ ወጪ እንዳይበዛባችሁም ከእንግልት ለመዳንም ከላይ የተዘረዘሩትን በባሶች ብትጠቀሙ አሪፍ ነው።

በplane መምጣት ለምትፈልጉ ደግሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድን በመጠቀም በደቂቃዎች ውስጥ ጎንደር አየር ማረፊያ መድረስ ይችላሉ። it takes only 41 min ፤ ዋጋው ከ1800 - 2500 ድረስ ኢትዮ አየር መንገድ ያስከፍላል ።

የአየሩ ሁኔታ

ጎንደር በሰሜን ኢትዮጵያ ስለምትገኝ በጣም ከፍታ ቦታ ላይ ነች። ይህም የጎንደርን አየር ቀን ቀን ፀሐያማ መሸት ሲል ደግሞ ብርዳማ እንዲሆን አድረጎታል so ከቤታችሁ ስትመጡ ሹራብ ነገር ብትይዙ ይመረጣል።

የካንፓሶች ብዛት

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በዋናነት አምስት ጊቢዎች አሉት ፦ እነርሱም

1, GC ግቢ <health science college>

2. Fasil ግቢ <Engineering science>

3. ቴዲ <all natural science> except eng. Science, health science, and agr. Science.

4. ማራኪ ግቢ< all social science>

5, ጤዳ ግቢ<agricultural science>

ማራኪ ፤ ቴዲ ቨተርነሪ እና ፋሲል ጊቢ የተያያዙ ጊቢዎች ሲሆኑ ጠዳ እና Health ጊቢ ደሞ የተለየ ቦታ ነው ያሉት ።

የዕቃ ስርቆት ጉዳይ

ማስ ጠን ቀ ቂ ያ ከመናኸሪያ ወደ ግቢ በምትሄዱበት ወቅትና ግቢ ከገባቹህ በኋላ ወደ ከተማ ምናምን ስትወጡ ንብረቶቻችሁን በንቃት መጠበቅ ይኖርባቹሃል ምክንያቱም ከተማው ላይ አዲስ ተማሪዎችንና የግቢ ተማሪዎችን የሚሰርቁ የተደራጁ ሌቦች አሉ ።

የትምህርት ዘርፎች

❄ Health science college በሀገራችን ቀደምት ከመሆኑ የተነሳ በሀገርቱ ካሉ universityዎች አሪፍ የሚባል የትምህርት አሠጣጥ አለው ፤በhealth science college የተዋጣለት ግቢ ነው ።

Engineering science የተከፈተው በቅርብ ጊዜ ቢሆንም እንኳ በሀገራችን ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች የመጀመርያውን ደረጃ የሚይዝ campus ነው።

በውስጡ 8 የተለያዩ departments አሉ ፦

1. Electrical and computer Engineering
2. Biomedical Engineering
3. Chemical Engineering
4. Mechanical Engineering
5. Civil Engineering
6. Construction management Engineering (cotem)
7. Industrial Engineering
8. Hydraulics Engineering

ሲሆኑ ምናልባት ቀጣይ አመት የሚጨመሩ departments ይኖራል የሚል ተስፋ አለ።

በተጨማሪም ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በ Engineering science ለተከታታይ 3 አመት ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች 1ኛ በመውጣት ሃትሪክ ሰርቷል።

ዩንቨርሲቲው በጤናው ዘርፍ የካበተ ልምድ እና ዝና ያለው ሲሆን ደግሞ ለtechnology(engineering and CS) more ትኩረት እየሰጠ ይገኛል።

first semester engineering courses ፦

1.Applied one ( maths guide book ካላቹህ እንዳትረሱ)

2.mechanics

3.Drawing(drawing material እንዳትረሱ)

4.Communicative( English)

5.Civics

6. Engineering profession

የካፌ ምግብ

ጣፍጦም ባይሆን ይበላል ፤ ምንም አይልም ቀን ቀን አላቸው የሚደብሩ ምግቦች የሚቀርብበት ...!

ከካፌ ውጪ ስላሉ ምግብ ቤቶች

Non ካፌ ተማሪዎች ፋሲል ግቢ ውስጥ ወደ 4 ላውንጆች አሉ ፤ከአራቱ ላውንቾች ውስጥ አንዱ አሪፍ ሚባልው 600 ብር አከባቢ ወርሃዊ ኮንትራት ነው ምሳ እና እራት ብቻ ያካተተ ኮንትረት ነው ።

ፋሲል Launge ፦

1. በየአይነት 12- 15 birr
2. ሽሮ 16 birr
3. የፍስክ ምግብ ከ25-35birr

መምህራን launge ፦

1. የፆም ከ25-35 ብር
2. የፍስክ ከ20-50 ብር

ዋና launge ፦

ይህ ምግብ ቤት ዋጋው ከመምህራን ላውንጅ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ምግባቸው ግን 1ኛ ነው ።

ሸንት ቤት

አሪፍ ነው ፤ ምንም አይልም .!

ውሃ ፤ መብራት ፣ WIFI

WIFI በጣም ገራሚ ነው ፤ የትኛውም ካንፓስ በሌለ ፍጥነት ነው የሚሰራው ፤ ውሃ እና መብራት የሀገሪቷ ችግር ስለሆነ አንዳንዴ ይጠፋል የሚያሳስብ ግን አይደለም ።

# 5)ሀዋሳ_ዩኒቨርሲቲ

አድራሻ

ሃዋሳ ከአዲስ አበባ ቅርብ ርቀት ላይ የምትገኝ ውብ ከተማ

የሲዳማ ክልል ፈርጥ ስትሆን የመናገሻ ከተማም ነች ።

የአየር ሁኔታ

ብዙ ግዝ በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሞቃታማ ሁና አመሻሽ ላይ ደስ የሚል አየር አላት ፤ ከተማዋ በራሱ የሆነ ደስ የሚል ነገር አላት ።

የካንፓሶቹ ብዛት

በውስጡ ያሉ ግቢዎች ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ በውስጡ ብዙ ግቢዎች ያሉ ሲሆን ከነሱም ውስጥም ጥቂቱን እንይ ፦

Main campus

Location: Hawassa town (found on the enterance of the city)

ዲፓርትመንት

governance

Engineering

social others

art

architect

touris

hotel management

Sport

law

Computational science ..

Techno campus ፦

Location:beside the main campus connected with the main campus though bridge ፦

ዲፓርትመንት

--> Engineering

--> information system

--> programming

--> Enla,discrit,

--> for engineering and computer science students until 3rd year wait here after that the student will be transfered to main campus..!

Agri campus

Location: located on the middle o fthe city around piyasa

ዲፓርትመንት

--> animal

Yirgalem campus

Location: Yirgalem town (near hawassa city..)

ዲፓርትመንት

FB faculty of business -

marketing management

logistic

Accounting

Cooperative

management

economics

5 Referral campus

Location:

located around the lake hawassa amazing view from the dorm nice sunset ...

ዲፓርትመንት ፦

--> Medicine

--> HO

--> nursing

--> environmental health

--> radiology

--> ophtometry

--> psychiatry

ወንዶ ገነት  agriculture

Location:wendo genet

Dep'  --> plant...

ውሃ፤መብራት፤ WIFI

መብራት እና ውሃ አይጠፋምኀለአንዳንድ ግቢዎች ለልሎች ይጠፋል ። አሪፍ የሆነ WIFI በግቢ የተለያየ ቦታ ላይ ይገኛል ።

ስለ ዮኒቨርሲቲው

ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሀገራችን ላይ አሉ ከሚባሉ ዩኒቨርሲቲዎች በትምህርት ጥራቱም ሆነ በግቢ ውበቱ አንደኛ ደረጃ ከሚባሉት ተርታ የሚመደብ ግቢ ነው።

ትምሮ በተወሰነ መልኩ ሊያጨናንቅ ይችላል ግን በግቢው ውበትና በከተማው ማብለጭለጭ

ካልተሸነፋቹህ የትምህርቱ ነገር ሙድ አለው።

የካፌ ምግብ

በጣም ጥሩ የሚባል ምግብ ያቀርባሉ ..!፤ ከብዙ ዮኒቨርሲቲዎች ጥሩ ምግብ የሚሰጥ ካንፓስ ነው ።

ከካፌ ውጪ ያሉ የምግብ ቤቶች ዋጋ

የምግብ ዋጋ በaverage ከ25-40 ብር ይደርሳል፥ የሁሉም ግቢዎች ዋጋ ይለያያል ።ቡና ምናምን 5 ብር

ለተማሪዎች fair በሆነ ዋጋ የሸጣሉ ትንሽ ቢወደድም ።

ሽንት ቤት

ጥሩ የሚባል ሽንት ቤት አለው ፤ ከብዙ ግቢዎች የሚሻል አይነት ባኞ አለው ።

## ባህርዳር_ዩኒቨርሲቲ

አድራሻ

ከአዲስ አበባ 530ኪ/ሜ ርቀት ያለው ሲሆን በባስ   የዘጠኝ ሰዓት መንገድ ነው (500ብር) ፤በ#Plane✈ የ45 ደቂቃ መንገድ ነው(2400ብር)..!

የአየር ሁኔታ

ሞቃታማ ነው  ቀን ቀን በጣም ፀሀያማ ነው በጣም፤ በተለይ engineering, Low,Arc,Land ያሉበት የባብ campus ይባላል ፤ ጥላ ያስፈልጋል ወንድም ሴትም ነው እዛ ጥላ የሚይዘው ጣጣ የለውም። እና ያው የሚሞቅ ነገር አያስፈልግም ቀለል ያለ ብርድ ልብስ  ለመያዝ ሞክሩ።

የካንፓሶች ብዛት

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ  7 ካምፓሶች አሉት  ፤ አራቱ ከተማ ውስጥ ሶስቱ ደግሞ ትንሽ ከከተማ ወጣ ይላሉ።

በውስጡ ያሉ ግቢዎች ሰባት ሲሆኑ እነርሱም ፦

ፔዳ ግቢ

ዋናው ግቢ  ሲሆን በውስጡም 2 ግቢ አሉት faculty of Business(Fb) ena main ይባላሉ ።  የተለያዩ የትምህርት መስኮች ይሰጣሉ የሚገኘው ከከተማ 2ብር ባጃጅ ነው ያው ከተማ በሉት ።

በውስጡ ያሉ የትምህርት መስኮች ፦

- all social dep'ts exept law and Governance
- Comptional science
- medcine
- Maritaym

ሰላም ግቢ

ይሄም ከተማ ነው የሚገኘው ከዋናው ግቢ ብዙም አይርቅም የናቹራል ግቢ ነው ።

Textile ጋር የተያያዙ ሁሉም departmenቶች እዚህ ግቢ ላይ ይገኛሉ ።

ይባብ ግቢ

ይሄ ግቢ ሞቃታማ እና ፀሀያማ ነው የሚገኘው ባህርዳር መግቢያ ላይ ነው ከከተማ የወጣ ነው ።

በውስጡ ያሉ የትምህርት መስኮች ፦

fresh Engineering

computer science

Law

Arc

Land organisation ናቸው

Architecture በፈተና ነው ሚገባው ፥ በየአመቱ ሰላሳ ተማሪ ተቀብሎ ያስተምራል ከአንደኛ አመት ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ በዚሁ ግቢ ይማራሉ።

ዘንዘልማ ግቢ

ይህ ግቢ ደሞ ከዩኒቨርስቲው መውጫ ላይ ነው ያለው ። በውስጡ ያሉ የትምህርት መስኮች ፦

agriculture

ke compitional Geology dep't

vertenary medicine et..

ፖሊ ግቢ

fresh የለበትም ያው 2nd year እና 3rd year

engineering ነው ያሉት ። አሪፍ ግቢ ነው የሶሻል ትምህርቶች ይሰጥበታል ..!

አጠቃላይ ባህርዳር ዮኒቨርሲቲ በ5 ዲፓች ተደራጅቷል ፤ እነርሱም ፦

Faculty

Colleges

Institutes

Schools and

Academy ናቸው ።

Institutes

Bahir Dar Institute of Technology

Ethiopian Institutes of Textile and Fashion

Technology and

Institute of Land Administration

Colleges

College of Agriculture and Environment

College of Medicine and Health Sciences

College of Business and Economics and

College of Natural sciences

Schools

School of Law

School of Computing and Electrical Engineering

School of Civil and Water Resources Engineering

School of Mechanical and Industrial Engineering and

School of Chemical and Food Engineering

Faculties

Educational and Behavioural Sciences (the oldest),

Faculty of Humanities, and

Faculty of Social Sciences

Academy

Maritime Academy

Sports Academy

የካፌ ምግብ ...

ምንም አይልም በተለይ ዳቦው በጣም ነው ደስ የሚለው ሁሌም ዳቦ አለ ።

ከካፌ ውጪ ያሉ ምግቦች

ለተማሪ በጣም ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ የተሻሉ ምግቦች ይቀርባሉ ፤ዋጋቸው በጣም ጥሩ የሚባል ነው ። ዋጋቸው ከታች ተዘርዝሯል ...

ፍርፍር በቀይ በአልጫ፣ ሽሮ፣ በየአይነት፤ ፓስታ፣ ድንች፣ እንቁላል ሳንዱች ሥጋ ፍርፍር ጥብስ ዋጋው ከ 15-35 ብር ብቻ ይገኛሉ ።

ሻይ ከ1ብር እሥከ 2.50 እና ቡና ከ 2 ብር -3ብር

ለስላሳ 10 እና 12 ብር ይገኛል ።

የሸቀጥ መሸጫ

ሱቅ የፈለጋችሁት ነገር አለ ግቢው በር ላይ ብዙ ሱቆች አሉ ምንም ነገር ፈልጋችሁ አታጡም ። ውጭ በር ላይ ደግሞ ያበደ ነው ቡና ፣ሻይ ፣ወተት፣ ምግብ ቤቶች ጨቅ ናቸው ።

የሚሰጡት ኮርሶች

ትምህርትን በተመለከተ Almost ሁሉንም የትምህርት መስኮች ይሰጣል ፤ የሚቀረው ዘርፍ የለም  ነገር ግን በጤና ሳይንስ ውስጥ HO, Dental and Radiology ትምህርቶች የሉም ።( ዘንድሮ ከተጨመረ አላውቅም ) በተረፈ  ፤ Medicine, Pharmacy, Nursing በግቢው ይሰጣሉ ።

ውሃ ፣መብራት እና ዋይፋይ

ሁሉም በጣም አሪፍ ነው ።(  ትንሽ ውሃ ያስተቸግራል ግን ይለመዳል ) ፤ ይባብ ግቢ ውሃው አንዳንዴ ጨዋማ ነው  ።

የዶርም ሁኔታ

ትንሽ ዶርሙ ሰፊ ነው እስከ 12 ተማሪ በአንድ ዶርም

ይመደባል ። ያ ትንሽ ያስጨንቃል የዶርሞቹ ጥራት ለክፉ አይሰጥም ...!

የፀጥታ ነገር

ትንሽ የፀጥታው አንዳንድ ግዜ ይታወካል ፤ ነገር ግን ከብዙዎቹ ግቢዎች የተሻለ መረጋጋት አለው ።

====================

# 7)Mekele_university

አድራሻ

በትግራይ ክልል ከአዲስ አበባ በ600 km አከባቢ ርቀት የምትገኝ ከተማ ነች መቀሌ ።በመኪና=750 ብር ፤ በplane=2800 ብር ነው::

የአየር ሁኔታ

ሞቃታማ የምትባል ከተማ ነች ፤ በብዙ መልከ ደስ የሚሉ ህዝቦች ያሉባት ምርጥዬ ከተማ ናት ።

የካንፓሶች ብዛት

በመቋሌ ዮኒቨርሲቲ 6 campus ኣሉ።

Social campus(ይሄ አዲ ሃቂ በሚባል ሰፈር ስለሚገኝ ወደ ፈለግከው ለመሄድ በጣም ኣመቺ ነው ። በቃ ራሱ ከተማ ማለት ነው ።

veterinary campus ፦ ይሄ ከከተማው ራቅ ይላል የህክምና ነክ ትምህርቶች የሚሰጡበት ግቢ ነው ።

mit (ይሄ ግቢ ተፈትነህ ነው ምትገባው እና ትንሽ ተማሪ ነው ሚቀበሉት ለቀለም ተማሪዎች ይመከራል)( ከ astu ጋ ተመሳሳይ ነው..!)

arid ፦ የኣዘር ኣግሪ ግቢ ነው ግን በጣም ትልቅ ነው ።

ayder የmedicine ግቢ ነው ።

quiha ፦ የengineering ነው እና ኣዲስ ነው ከ ከተማ ትንሽ ራቅ ይላል ሁሉም ነገር ንፁህ ስለሆነ ደስ ይላል ።

የካፌ ምግብ

ምንም አይልም ፤ ለክፉ አይሰጥም ጥሩ የሚባል ትምህርት ጋር ስለሆነ በምግብ ብትጎዱም በማስተማር ይኩሳቹሃል ።

የካፌ ውጪ ያሉ ምግቦች

ምግቦች ብዙ ውድ አይደሉም በአማካኝ 20-30 ብር ናቸው ። ከካፌ በተሻለ ጥራት ማግኘት ይቻላል ።

የውሃ ፤ መብራት ፤ WIFI

ውሃ በጣም ችግር ነው ለወር ገላችንን ሳንታጠብ አሳልፈን እናውቃለን ፤ ከተማዋ ላይ የውሃ ችግር ስላለ እዚም ያስቸግራል ። መብራት ጣጣ የለም ፤ ሁሌም አለ ፤ wIFi እንደ አቅሚቲ ለማስገባት ተሟክሯል ፤ መሻሻል ቢገባውም ያን ያክል የከፉ አይደለም ።

ሽንት ቤት

ጥሩ ነው በንህፅና ለመያዝ ይሞከራል ፤ የውሃው ነገር እክን ቢሆንም የተሻለ ነገር አለው ።

8)ሀረማያ_ዩንቨርሲቲ

አድራሻ

ሀረማያ ከሀረር 17ኪ/ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ወይም ሀረር ከመግባታችን በፊት የ10ብር መንገድ ሲቀረን ያለች ከተማ ናት ሃረማያ ለድሬም ቅርብ ናት የ25ብር  መንገድ ብቻ ነው ።

የአየር ሁኔታ

ብርዳማ ነው በተለይ ምሽት ላይ በጣም ይበርዳል

ሀረማያ ሀሩር ነው ምናምን የሚባለውን አትስሙ በርግጥ አንዳንድ የሙቀት ወራት አሉ ግን ብዙውን ጊዜ ቅዝቃዜው ያመዝናል ፤ ስለዚህ ወፍራም ልብስ መያዝ ይኖርባቹሃል ። ብርድ ልብስ ምናምን መሸከም ካልፈለጋቹህ ሀረማያ ልብስ እና አንዳንድ ሸቀጦች ርካሽ በመሆናቸው ግቢ ከገባቹህ በኋላ መሸመት ትችላላችሁ ።

የካንፓሶች ብዛት

በውስጡ ያሉ ግቢዎች አንድ ትልቅ ግቢ ሆኖ በውስጡ ግን ሶስት የተያያዙ subግብዎች አሉት በተጨማሪም ሀረር ከተማ ላይም ሌላ ግቢ አለው ።

Subግቢዎች ፦

1 Main campus

All social departments

Computer science

Business

Economics

Natural computational science

Law

Teaching and

Agriculture....

Gandajay.........(Techno campus )

Engineering above second year

Food science

Station

Fresh Engineering students and

Veterinary

Hareri

Medicine

Health

Pharmacy

ግቢው ውስጥ አሪፍ የሚባሉት agri,law and computer science ናቸው ።

የካፌ ምግብ

የካፌ ምግብ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች

መካከል ቀዳሚው ነው ፤ በሳምነት 5 ግዜ ስጋ ያለው ብቸኛው ግቢ ነው ። የካፌ ምግብ አያሳስብም…!

ምሳ ፦

በሳምንት አምስት ቀንTherefore አለ ፤ 1 ቀን ፓስታ1 ቀን ደግሞ ፤ መኮረኒ ነው ።

ቁርስ ፦

ሳንድዊች 1 ፤ ማርማራታ ፤ ዳቦ በስጋ ፤ ፍርፍር በሩዝ በዳቦ …ብቻ ያበደ ነው ።

ከካፌ ውጪ ያሉ ምግቦች

ካፌ ያበደ ምግብ ስላለ የውጪ ተመጋቢ አናሳ ነው ፤ ውጪ መመገብ ከፈለጋችሁም በተመጣጣኝ ዋጋ 15-20 ጥሩ ምግብ ማግኘት ትችላላችሁ ።

ጫት እና ሃረማያ

የጫት ነገር የማይሆንላቹህ አልያም ጫትን እንደ ምግብ የምትጠቀሙ ተማሪዎች ስለምትኖሩ ሌላ ግቢ ሄዳቹህ እሰጥ አገባ ውስጥ ከመግባትና ብሎም የዲሲፕሊን ኮሚቴ ጋር ከመጨቃጨቅ ሀረማያ ዩንቨርሲቲ ጎራ ብትሉ ጥሩ ነው ። ( ጫት መቃም አይካበድም እንደ ህግ ግን ክልክል ነው )

አደራችሁን ከጫት ለመራቅ ሞክሩ ፤ በተለይ ለጫት አዲስ የሆንችሁና ምናልባትም ከነ ጭራሹ የማታውቁት ፍሬሽ ተማሪዎች ከተማው ላይ ባለው የጎላ የጫት ተጠቃሚነት እንዳትረበሹ ብሎም እንዳትሞክሩት ለማሳሰብ እወዳልሁ።

ውሃ ፤ መብራት ፤ WIFI

የውሃ ችግር የለብንም ቢጠፋ ቢጠፋ እንኳ ካፌ አይጠፋም ስለዚህ ከካፌ መጠቀም ይቻላል ግን አይጠፋም ፤ ለሴቶች በየብሎካችው ውሃ አለላቸው ፤ መብራትም በፍፁም አይጠፋም ፤ WIFI ጥሩ ነው እየቸሻሻለ ነው የሚገኘው..

ረብሽ እና ሃረማያ

ሃረማያ ዩንቨርሲቲ የሚመደብ ሰው የብሄር ቀልድ ምናምን እንዳይቀልድ በጣም Serious ጉዳይ ነው ፤ ባሁኑ ሰዓት የትኛውም ግቢ የሚገባ ተማሪ ከዘረኝነት የፀዳ ካልሆነ አዛ ነው። እኛ ጋር ግን ባስ ይላል ብሄርተኝነት ምናምን ....F ነው ግሬዱ።

የዕቃ ስርቆት

በተረፈ ዝርፊያና ሌላ አስጊ ሁኔታ የለም ፤ ከተማዋ ጭንቅ በማይወዱ ፍቅር በሆኑ የሀረር ልጆች የተሞላች ነች ።

ሽንት ቤት

የሃረር ሰው ጭንቅ የለበትም ፤ ጥሩ የሚባል ሽንት ቤት አለ አያጨናንቅም ።

# 9)ወሎ_ዩንቨርሲቲ

አድራሻ

አማራ ክልል በደሴ ከተማ የምትገኝ የፍቅር ሀገር ነች ወሎ..!

የግቢ ብዛትና የአየር ሁኔታ፡ ዩንቨርሲቲው ሁለት ግቢዎች ያሉት ሲሆን እነሱም ደሴ ከተማ እና ኮምበልቻ ከተማ ላይ ይገኛሉ፤ ሁለቱ ከተሞች በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኙ ከተሞች ቢሆኑም የአየራቸው ፀባይ ግን ለየቅል ነው።

የአየር ሁኔታ

ደሴ ከተማውም በመጠኑ ብርዳማ ሲሆን ግቢው ደግሞ ትንሽ ከከተማው ወጣ ብሎ ስለሚገኝና ሰፈሩም ዛፍ ነገር ስላካበበው የብርዱ መጠን ጠንከር ይላል በተለይ ምሽት ላይ ወዝወዝ ያስደርጋል ።

ኮምበልቻ ከተማ ደግሞ የኢንዱስትሪ ከተማ ስለሆነች መሰለኝ ሞቅ ትላለች ምናልባት የፋብሪካው ጢስ ይሆን ለማንኛውም ኮምቦልቻ ግቢ ለምትመደቡ ተማሪዎች ቀን ቀን ሞቃታማ ማታ ማታ ደግሞ ከዶርም ወጣ ሲሉ ብርዳማ ግቢ ነው ።ኮቻ ግቢ ልክክ በልክ ነገር ናት ማለት ግቢው በጣም ሰፊ ሚባል ነገር አይደለም geographical አቀማመጡ ለተማሪዎች ሳይሆን ለወታደሮች ተብሎ design የተደረገ ሊመስላቹህ ይችላል ቢሆንም ግን ፍቅር ፍቅር ከሚሸቱት የግቢው ማህበረሰብ (ተማሪዎች) ተመጣጣኝ

ካሳ ይጠብቃቹሃል።

የካንፓሶች ብዛት

ደሴ campus (main campus)

ሁሉም የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች የሚገኙበት ሲሆን በተጨማሪም ከተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስኮች ውስጥ የጤናውን(medicine, nursing,HO..) እና የቲቺንግን(biology, physics, chemistry..) እና የቋንቋ ትምህርት (አረብኛ፣አማርኛ..)ክፍሎች የያዘ ግቢ ነው።

kombolcha institute of technology

ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ግቢው የቴክኖሎጂ ግቢ ነው ። በውስጡም ፦

Engineering, computer science, fashion design and architecture የመሳሰሉትን መስኮች አቅፎ የያዘ ግቢ ነው ።

Engineering፦

Electrical and computer engineering

Mechatronics Engineering (robotics)

Software engineering

Mechanical Engineering

Civil engineering

Textile engineering

water resources and irrigation Engineering

Hydrolics Engineering

Industrial Engineering

Cotem

Garment Engineering

Leather Engineering

Chemical engineering...

በቀጣይ ምናልባትም Biomedical engineering ሊጀምር ይችላል።

C omputer science

#CS

#IS

#IT

Fashion design and architecture

የትምህርት ሂደቱ አሪፍ የሚባል ነገር ነው ቢሆንም ግን ትንሽ ያጨናንቃል ።

የዮኒቨርስቲው ሁኔታ

በግ ተራ፣ኦቨር፣ጨብሲ ምናምን ለሚያበዛ ተማሪ የግቢው የክብር መሸኛ ደብዳቤ ይበረከትለታል ( ትምሮ ፊት ይነሳዋል) በተረፈ ግቢያችን ከዘረኝነት የፀዳ ነው እንዳልል ከኢትዮ ውጭ ያለ ዩንቨርሲቲ ስለሚያስመስልብኝ በአንፃራዊነት ከሌሎች ግቢዎች በተሻለ መልኩ ሰላማዊ ግቢ ነው ለማለት ይቻላል።(ኮሽ ብሎ አያቅም.. ) ኮምቦልቻ ግቢ ለምትመደቡ ተማሪዎች ግቢው የሚገኘው አስፓልት ዳር በመሆኑ ግቢ በር ላይ በመውረድ ከመናህሪያ ትርምስ ትድናላቹህ ።

የዕቃ ስርቀቶ

ደሴ ግቢ ለምትመደቡም ሰርቪሶች ስለሚመደቡ ብዙ አታስቡ ፤ለማንኛውም ግን ንብረታችሁን ጠንቀቅ በሉ ምክንያቱም መናህሪያ መግባታቹህ ስለማይቀር ብዬ ነው። ወሎ ዩኒቨርሲቲ ስትደርሱ የተማሪዎች ህብረት ፣ የተማሪ ፖሊስ፣ቻሪቲ ክበብ፣ የሰላም ክበብ .. ወዘተ አባላት በር ላይ ባጅ አጥልቀው ስለሚቀበሏቹህ ምንም ዓይነት ሀሳብ አይግባቹህ ።

ውሃ ፤ መብራት ፤ WIFi

በመብራተ እና ውሃ የሚታማ ግቢ አይደለም ፤ ትንሽ WIFI ነው ። እሱም ቢሆን ምንም አይልም ..

ሽንት ቤት

በጣምም ደስ ባይል እንደሌሎቹ አይደለም ፤ በአንፃራዊነት በጣም ጥሩ ነው ።

# 10)አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ

አድራሻ

Heaven of rift valley ይሏታል ፤ ብዙ መዝናኛዎች የያዘች ሀገር ናት ሁለት ሀይቆች አሏት Abaya and Chamo መገኛዋ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲሆን ከአዲስ አበባ 515KM ርቃ ትገኛለች ። ዩኒቨርስቲው ከተመሰረተ 34 አመታትን አስቆጥሯል ።

የአየር ሁኔታው

ሞቃት ነዉ እና ቀለል ያሉ ልብሶችን ብትይዙ ይመረጣል ፤ አርባምንጭ ሲባል ብዙዎቻቹህ አረንጓዴ ስለሆነች ብርዳማ ናት ምናምን እንዳትሉ ገራሚ ሙቀት ነው የሚጠብቃችሁ ..!

ከካፌ ምግብ ውጪ ያሉ ቤቶች

በጣም ምርጥዬ ክበብ አለ በተመጣጣኝ ዋጋ ቀላል ምግቦች ይሸጣሉ ፤ ለየአስተማሪዎችም የተሰራ መመገቢያ አለ ትንሽ ከሌሎቹ ቢወደድም ምርጥ የሆነ ምግብ ይሰራሉ ።

ፍራፍሬ እና አርባምንጭ

ከተማዋ ባጠቃላይ በፍራፍሬ የተሞላች ናት

ሙዝ

ማንጎ

አፕል

አቮካዶ .....መገለጫዋ ናቸው ።

ዮኒቨርስቲው በ6 campus ይከፈላል ።

1 የመጀመሪያው main campus ሲሆን

Arba minch መግቢያ ላይ ይገኛል

-Engineering እና

-Computer science

ብቻ ነው እዚህ ግቢ የሚሰጡት ፊልዶች ።

2 ሌላኛው Chamo Campus ይባላል social science ፊልዶች ብቻ ነው እዚህ ግቢ ያሉት Like

-Law⚖⚖⚖⚖⚖

-Business and Economics

-Accounting

-political science

የመሳሰሉት ይሰጣሉ ።

3 ሶስተኛው ግቢ ደሞ ነጭ ሳር Or Health Campus ሲሆን ያው የጤና ፊልዶች እዛ ነው ያሉት ፦

- Medicine

-Other Health

-HO

4 Abaya campus

both Natural and social science Computational የደረሳቸው እዚ ነው የሚማሩት ።

5 አምስተኛው ደግሞ Kulfo campus ይባላል የ Agriculture ተማሪዎች campus ነዉ ።

6 ስድስተኛው Sawula campus ይባላል ከአርባ ምንጭ ከተማ የ4 ሰዐት ያክል መንገድ ነው ጎፋ ዞን ሳውላ ሚባል ከተማ ላይ ነው ሚገኘው ።

ከnatural Engineering Like ፦

-Half Civil engineering

-Hole Food engineering

-Hole Automotive engineering ✈

-Hole Electro Mechnical

በengineering ስር የሚሠጡ ፊልዶች ፡-

-Civil engineering

-software engineering

-Architecture engineering

-Electrical and computer engineering

-Mechanical engineering ⛓⚙

_ metal and production engineering

- metrology and hydrology

- electromechanical

_food engineering

-Hydroelectric engineering

-Environmental engineering▲

-Water supply engineering⛱

ግቢው በhydrolic ከምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ቀዳሚ ነው።

የካፌ ምግብ

ምግቡ በጣም ደስ ይላል፤ ጥሩ ነው በተለይ ምሳ እና ራት ምንም አይልም ቁርስ ግን ትንሽ ...ግን ከብዙ ግቢዎች አንፃር በጣም ጥሩ ነው ፡፡

የዕቃ ስርቆት ጉዳይ

ትንሽ ያስቸግራል ከተማ ምናምን ለመዝናናትና ለሽመታ በምትንቀሳቀሱበት ጊዜ መጠንቀቅ ይኖርባቹሃል ፡፡

ሸንት ቤት

ምንም አይልም በየቀኑ ስለሚፀዳ ከሌሎች ግቢዎች ቢሻልም ምርጥ የሚባል  አይደለም ።

ውሃ ፣ መብራት WIFI

ውሃ በየቀኑ ይለቀቃል ችግር የለም ፣ መብራትም አያሳስብም ፣ WIFI በቾሻለ ደረጃ አለ አንዳንድ ዶርሞች ውስጥ ድረስ ይሰራል ።

# 11)Arsi university

አድራሻ

ኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከአድስ አበባ የ85ብር መንገድ ነው ፤ ከአዲስ አበባ በጣም ቅርብ ዩንቨርሲቲ በመሆኑ ለአዲስ አበባ ተማሪዎች አመቺ ነው ። (አልፎ አልፎ ለመመላለስ.... )

የአየር ሁኔታ

ጥቅምት አካባቢ በተለይ ማታ ማታ በጣም ይበርዳል ፤ ከጥቅምት ህዳር ውጭ ያሉ ወራቶች አየሩ በጣም ተስማሚ ነው ።

የካንፓሶች ብዛት

በውስጡ ያሉ ግቢዎች አራት ናቸው ፤ በስራ ላይ ያሉት የሁሉም መገኛ አሰላ እና በቆጂ ከተማ ላይ ነው ። ግቢዎቹም ፦

Dinsho፡አሰላ ከተማ መግቢያ ላይ ይገኛል

በውስጡም ፥competitional and natural science ይሰጣል ።

Ardu፡ ከመናሀሪያው የ5ብር ባጃጅ መንገድ ነው

በውስጡም ፡ ከሁለተኛ አመት በላይ ያሉ የlaw,accounting.marketing. ተማሪዎች ይገኛሉ፤ በተጨማሪም Agri ተማሪዎችም ይገኙበታል።

Bekoji ፡ በቆጂ ከተማ ላይ የሚገኝ ግቢ ሲሆን በውስጡም የsocial science ተማሪዎችን ያስተምራል።

Health campuass ፡ በጊዜያዊነት የሚማሩት TTC በሚባል teachers college ነው

በውስጡም  Ho, midwify, nursing helth ተማሪዎች ይማራሉ,።

Medicine ተማሪዎች የሚማሩት በአሰላ ሆስፒታል ውስጥ ነው ፤ ሌላው ምናልባት ቀጣይ አመት ይጀምራል ተብሎ የሚጠበቅ ትልቅ ግቢ አለ

ይህ ግቢ በቀጣይ ዓመት ተማሪዎችን የሚቀበል ከሆነ አርሲ ዩንቨርሲቲ ለመጀመሪያ ጊዜ Engineering ክፍል ይኖረዋል ማለት ነው። እስካሁን ግን አርሲ ዩንቨርሲቲ ምህንድስና ክፍል

የለውም ።

ኮፒ በጣም ርካሽ ነው ፤ ግቢ ውስጥ 35 ሳንቲም ከግቢ ውጭ 50 ሳንቲም ነው ።

ካፌ ምግብ

አብዛኛው ተማሪ ካፌ ተጠቃሚ ነው ፤ የካፌው እንጀራ አንደኛ ነው አያሳስብም (ardu campus )

አርዱ ካምፓስ ውስጥ ከአርብ እና ከእሮብ ውጭ እራት ስጋ ነው (therefore) ፤ ቁርስ ደግሞ ከሃሙስና ማክሰኞ በስትቀር ሁሌም ፍርፍር ነው፡ ሀመስ ግን ሩዝ ነው ፤ ማክሰኞም ይው ፍርፍር ነው ግን ስጋ ፍርፍር ነው ።

ካፌ ውጪ ያሉ ምግቦች

ላውንች (የውጪ ምግብ ) ግን ብዙም አይነፋም ተማሪውም

ለላውንች እምብዛም ነው ፤ ብዙ አይጠቀምም ፤ ሻይ 2 ብር ፤ ቡና 5 ብር ፤ ወተት 4-5 ብር ነው ። የግቢው የተማሪ ላውንች ምግብ በየአይነት 15ብር ፤ ፍርፍር 15 ፤ ፓስታ 15 ፤  በብዛት 15 ብር ናቸው ፤ ምግቡ ግን  ትንሽ አሪፍ አይደለም..!

## የዶርም ሁኔታ

ዶርም ለፍሬሽ ሴት ተማሪዎች ለብቻቸው ነው ፤  ማለት ከነባር ተማሪዎች ተለይተው ስለዚህ ብዙም አይረበሹም ፤  በተጨማሪም ለደህንነት ምቹ ነው

የወንዶች ዶርም ግን ከነባር ወንድ ተማሪዎች ጋር የተቀላቀለ ነው ።  (አንድ ላይ ትኖራላቹህ ማለት አይደለም ግን በየቀኑ ትተያያላችሁ ትገናኛላችሁ ...!)

## የዕቃ ስርቆት

ኀበግቢው ዙሪያ ምንም ዓይነት አስጊ ሰፈር የለም ፤ ሰላማዊ የሆነች ከተማ ነች አሰላ ።

ውሃ ፤ መብራት ፤ WIFI

ውሃ እና መብራት አያሳስብም እንደተለመደው ነው ፤ አንዳንዴ ይጠፋሉ ፤ WIFI ያስቸግራል ፡፡

ሽንት ቤት

ጥሩ የሚባል ነው ፡፡ በቃ ከብዙዎቹ ግቢዎች ይሻላል ፡፡

# ◦◴●◉✿[12) Dilla University ]✿◉●◴

ዲላ ዩኒቨርስቲ ከአድስ አበባ 360ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን

የአየሩ ሁኔታ ሚካበድ ሙቀት የለም ግቢው በጣም አርንጓዴ ነው ግን ከግቢው ውጪ ፀሃይ አለ፤በተወሰነ መልኩ ሞቃት ነው ለመልመድ ግን አይከብድም

በውስጡ ያሉ ግቢዎች፡ ሶስት

Techno: Engineering, CS

Main :agree, physics... and

Tena gbi: social...

ትምሮ በጣም አይከብድም ግን እንድታጠኑ በትንሹ ለማጨናነቅ ይሞክራሉ ፤ በተረፈ እንደማንኛውም ግቢ ካልቸከልክ ትጫራለህ

የምግብ ቤቶች ዋጋ ባንፃራዊነት በጣም አሪፍ ና ተመጣጣኝ ነው ዋጋ 15−17 ብር ነው

የቡና ዋጋ ከ 3−5 ብር ነው በጣም አሪፍ የጩፌ ቡና ዲላ ይገኛል

የካፌ ምግብ ብዙም አይደለም፤ ከግቢ ውጭ ግን አሪፍ ምግብ ቤቶች አሉ ከ13ብር ጀምሮ

ፍርፍር በጣም ርካሽ ነው

ሙዝ  የአንድ ብር አምስት ፍሬ

ያው ኑሮ በ ዲላ ርካሽ ነው የተለያዩ ኮንትሮባንድ እቃዎች ይገኛሉ

ልብስ እና ጫማም በጣም ርካሽ ነው

ባጠቃላይ ትወዱታልቹህ

ውሃ መቼም አይጠፋም

ሻወር 24 ሰዓት መጠቀም ይቻላል፤ ዋን ለሜ ምንጭ እያለች ዲላ የውሃ ችግር አይታሰብም::::::

# 13)ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

አድራሻ

Denmark ማለትም ደብረማርቆስ በአማራ ክልል ም/ጎጃም ከአ.አ 313km ትገኛለች በጣም ውብና ያማረች ከተማ ነች ።

የአየር ጸባይ

ቀን ላይ ሞቃታማ ስትሆን ምሽት ላይ እና ጠዋት ላይ ትንሽ ቅዝቃዜ አለ ።

ከተማዋ

የታላቁ ደራሲ የሀዲስ አለማየሁ (ፍቅር እስከ መቃብር) እንዲሁም የበላይ ዘለቀ እና የ ዮፍታሄ ንጉሴ እናት ሀገር ስትሆን ህዝቦቿ ከቤተሰባችን በላይ አቅፈውና ደግፈው ፍቅር ሰጥተው ያኖሩናል ፤ ወደዚች ሀገር ሲመጡ ዘረኝነት የሚባል ነገር አይኑ ጠፍቶ ተቀብሮ ፍቅር የሚባለው ነገር ዘረኝነት መቃብር ላይ በቅሎ ታገኙታላችሁ ሌላ በማርና በጠላ አንታወቃለን ...! ዮንቨርሲቲው ከከተማው በ1km እርቀት ላይ ይገኛል የ 3 ብር ትራንስፖርት

ማለት ነው ።

የካንፓሶች ብዛት

ሁለት ግቢ አለን ዋናው ግቢና ቡሬ campas በነገራችን ላይ ቡሬ ከማርቆስ 115km ርቀት ላይ ትገኛለች ፤ ይህም የ50ብር ትራንሰፖርት ማለት ነው ።

የሚሰጣቸው ት/ቶች ሰንመለከት ፦?

የማይሰጠው የ ት/ት ክፍል የለም ግን በsocial በኩል እንደ markrting,banking & finance አይሰጥም ፤ መቼም ከዚህ ውጭ ምርጫ እንደማይኖሮ ተስፋ አደርጋለሁ....!

ውሃ ፤ መብሪት ፤ WIFI

ከነጉድለቶቹ ጥሩ የሚባል ነው ፤ ትንሽ WIFI ያሳስባል እዛ ነው እንጂ ለሌሎቹ ምንም አይሉም ..!

ሽንት ቤት

ምንም አይልም የተሻለ ነው ።

# 15)Debrebirhan University

አድራሻ

ደብረ ብርሃን ከአዲስ አበባ 130km ላይ ትገኛለች ከአንቦ ቀጥሎ ሁለተኛው ለአዲስ አበባ ቅርብ ዮኒቨርስቲ ነው ።

የአየር ሁኔታ

በጣም ቀዝቃዛ ነገር ግን ግንቦት አካባቢ ለቲሸርት አመቺ ነው ጠዋት እና ማታ ግን በየቀኑ ብርድ አይቀሬ ነው፡፤ ደብርዬ ውስጥ በተለይ ጥቅምት አብዝቶ ደሞ ሕዳር ላይ ያለው ብርድ እንኳን ለሰው ልጅ ለቁስም አይመከርም ፤ በጣም ከፍተኛ ብርድ አለ ስለዚህ ተማሪዎች እዚህ ከመጡ በጣም ወፍራም ብርድልብስ ወፍራም ልብሶች ግድ እና ግድ ነው።

የካንፓስ ብዛት

ሁለት ካንፓስ አለ ሚኒሊክ እና Main ካንፓስ ፥

Main campus ፦ ከከተማም የ 3ብር ታክሲ ነው ለከተማው ቅርብ ነው ፦ በስሩ ያሉ ኮሌጆች ዝርዝር ፦

ለናቹራል ፦

► Technology collage

➡ Computing

1 Computer science

2 Information system

3 information technology

➡ Engineering

1 Electrical and computer engineering

2 Mechanical engineering

3 Civil engineering

4 COTM (construction

technology management)

5 Industrial engineering

6 Chemical engineering

7 food engineering

8 software engineering

9 hydroelectric engineering

survey engineering

► Agriculture collage

1 Agro Economics

2 Animal science

3 plant science

4 Horticulture

5 Natural resource management

► Computational collage

1 Biotechnology

2 Geology

3 Mathematics

4 physics

5 Biology

6 Chemistry

7 Sport science

8 Statistics

Social Science :-

1 Management

2 Accounting

3 law

4 logistics

5 economics

6 English

7 Amharic

8 journalism

9 geography

History etc.....

ሚኒሊክ ካንፓስ ፦ መሃል ከተማ ነው ሚገኘው

በውስጡ የሚሰጡ ፊልዶች ፦

1 Medicine
2 Public health officer
3 Anasteisia
4 medical laboratory
5 Nursing
6 midwifery

የካፌ ምግብ

Main campus የምግብ ነገር ብዙም አያሳስብም በጣም ጥሩ የሚበል ምግብ ያቀርባሉ ፤ ከብዙ ግቢዎች የተሻለ እና

የጣፈጠ ምግብ አለ ።

ከካፌ ውጪ ያሉ ምግቦች

ለተማሪ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ጥሩ ምግብ ያቀርባሉ ፤ ምግብ በላውንች ከ12.00-22.00 ብር ነው ።ሽሮ ፤ተጋቢኖ ፤ፓስታ ፤ስልስ ፤ በአትክልት ፍርፍር ፤በየአይነት ፤ ቀይወጥ ፤ቅቅል ፤ ስጋ ፍርፍር በጥራት የሚገኙ ምግቦች ናቸው ።

ምግብ ከዮኒቨርስቲ ውጪ

